# ማነህ ባለተራ?

ማነህ ባለተራ?
ማነህ ባለተራ?
ፍትሕን የምትሻ
ለውጥን 'ምትጠራ?!
ኤርትራዊ ነህ ወይ?
ኢትዮጵያዊ ሀበሻ?!
ግፍ ያንገፈገፈህ
ፍትሕን የምትሻ?!
ተከተል እንግዲህ
በአንድነት ሁንና
የናይል ልጆች ፈለግ
የግብፆችን ዳና፡፡
ማነህ ባለተራ?
ማነህ ባለተራ?
ላቲናዊ ነህ ወይ?
-የቼ፥ ቼ ጎቬራ?!
ፍትሕን የምትሻ
ለውጥን 'ምትጠራ?!
ተከተል እንግዲህ
በአንድነት ሁንና
የማንዴላን መንገድ
የጋንዲን ሰብዕና፡፡

(አስራት አብርሃም)